# ቅዱስ ያሬድ

**የስሙ ትርጓሜ**

***ያሬድ*** ማለት ርደት፣ ወሪድ፣ ማለትም መውረድ ማለት ነው፡፡ ከአዳም ስድስተኛ በሆነው በመላልኤል ልጅ በያሬድ ጊዜ ደቂቀ ሴት ከደብር ቅዱስ ወደ ደቂቀ ቃየን ወደ ምድረ ፍዳ ስለወረዱ ያንን ለማስታወስ አባቱ መላልኤል ያሬድ ብሎታል፡፡ "ወጸውዐ ስሞ ያሬድሃ እስመ በመዋዕሊሁ ወረዱ መላእክተ እግዚአብሔር ውስተ ምድር እለ ተሰይሙ ትጉሃን፣ ስሙን ያሬድ ብሎ ጠራው በእርሱ ዘመን ትጉሃን ተብለው የሚጠሩ የእግዚአብሔር መላእክት (ደቂቀ ሴት) ከደብር ቅዱስ ወደ ምድረ ፍዳ ወርደዋልና ማለት ነው፡፡ መጽ ኩፋሌ 5፤፳1-፳2 በኢትዮጵያም ዳግማዊ ያሬድ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተነሥቶ ሰማያዊውን ልዩ ጣዕመ ዜማ ወደ ኢትዮጵያ የሚያወርድ ነውና ይህንን ለመግለጽ እግዚአብሔር አምላክ በእናቱ እና በአባቱ ላይ አድሮ ያሬድ እንዲባል አድርጓል፡፡ ምስጢሩ ልዩ ጣዕመ ዜማን ከሰማይ የሚያወርድ መሆኑን ያሳያል፡፡

***ያሬድ*** ማለት ንብ ማለት ነው፡፡ ንብ የማይቀስመው አበባ እንደሌለ ሁሉ ቅዱስ ያሬድም ከቅዱሳት መጻሕፍት የማይጠቅሰው የለም፡፡ ከንብ የተገኘ ማር ጣፋጭ ከመኾኑም በላይ ሰሙ መብራት ኾኖ ጨለማን አርቆ ብርሃን በማሳየት ደስ እንደሚያሰኝ የቅዱስ ያሬድም ዜማ ንባቡ ከምስጢሩ ጋር ተዋሕዶ ምእመናንን ደስ ከማሰኘቱም በላይ ለምእመናን ደስታን የሚያበስር፣ ኀይለ ቃሉ ጨለማ ከሕደትን የሚያርቅ ነው፡፡

***ያሬድ*** ማለት ረአዬ ምስጢር ነጻሬ ኅቡአት "ምስጢር ተመልካች፣ ምስጢር ገላጭ ማለት ነው፡፡" ረአዬ ምስጢር መባሉ የመላእክት ምስጢራት የነበሩትን ጸዋትወ ዜማ አምልቶ አስፍቶ ተናግሯልና፤ "ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን" (ከቅዱሳን መላእክት በሰማይ የሰማኹት ዜማ ምን ይረቅ! ምን ይጠልቅ !) እንዲል፡፡ ነጻሬ ኅቡአት መባሉ ደግሞ ኅቡእ (ስውር) የኾነ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የነቢያት፣ የሐዋርያትን ገድል አምልቶ አስፍቶ ስለሚናገር ነው፡፡

***ያሬድ*** ማለት እንዚራ፣በገና፣ መሰንቆ ማለት ነው፡፡ እነዚህ በስልት በስልት ሲመቱ ለሚሰማቸው ደስ እንዲያሰኙ፥ የያሬድም ዜማ በንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ አደባባይ በቤተ ክርስቲያን ሲሰማ መላእክትን፣ ሰውንና እንስሳትን ደስ ያሰኛልና፡፡

**ውልደት እና እድገት**

ቅዱስ ያሬድ ሀገሩ ኢትዮጵያ ትውልዱ አኩስም ነው፡፡ ሚያዚያ 5 ቀን 505 ዓ.ም ተወለደ፡፡ እናቱ ክርስቲና (ታውክልያ) አባቱ ይስሐቅ (አብዩድ) ይባላሉ፡፡ አባቱ የአክሱም ጽዮን ቄሰ ገበዝ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የብሉያትና የሐዲሳት መምህራንና ተማሪዎች የሚገኙት አክሱም ጽዮን ነውና የአኩሱም ቤተ ቀጢን (ቤተ ጉባኤ) መምህር የነበረው የእናቱ ወንድም አጎቱ መምህር ጌዴዎን ይባል ነበር፡፡ ቅዱስ ያሬድ የሰባት ዓመት ብላቴና በኾነ ጊዜ አባቱ ስለ ሞተ ከአጎቱ ዘንድ ሄደ፡፡ መምህሩም "ከዚህ የመጣህበት ምክንያት ምንድን ነው?" አለው፡፡ እርሱም "መጻሕፍት እማራለኹ ብዬ ነው የመጣኹት" አለው፡፡ መምህር ጌዴዎንም ዐቅሙንና ዕውቀቱን በመገመት ለተማሪዎች "በሉ ፊደል አስቆጥሩት" አላቸውና ትምህርቱን ጀመረ፡፡ ኾኖም ቃለ እግዚአብሔርን የመቀበል ችሎታው ደካማ ስለነበር ዐብረው የሚማሩትም ሕፃናት "ያሬድ ዕንጨት ስበር ውሃ ቅዳ" እያሉ አፌዙበት፤ቀለዱበት፡፡ አጎቱ ጌዴዎንም ከሕፃናቱ ጋራ ሊወዳደር ባለመቻሉና መዝሙረ ዳዊትን ማጥናት አቅቶት ወደ ኋላ

በመቅረቱ ከትምህርቱ ድክመት የተነሣ በጨንገር (በአለንጋ) ቢገርፈው ሕፃኑ ያሬድም በዚህ ተበሳጭቶና ተስፋ ቆርጦ ከአክሱም ከተማ ወጥቶ ወደ እናቱ መንደር ወደ መደባይ ወለል ሲጓዝ የኢትዮጵዊቷ ንግሥተ ሳባ እና የንጉሥ እስራኤል ሰሎሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ (እብነ ሐኪም) የተቀበረበት ቦታ ደረሰ፡፡ ለጥሙ ከምንጭ ውሃ ጠጥቶ ለድካሙ ከዛፉ ጥላ አረፈ፡

በምን ምክንያት ከጓደኞቹ በታች እንደኾነ ሲያስብና ሲያሰላስል፣ ሲያዝንና ሲተክዝ ከቆየ በኋላ እግዚአብሔር አንድ የሚያጽናና ምልክት አሳየው፡፡ ይኸውም ክሬዋሕ ከሚባል ዛፍ ሥር በውሃው ምንጭ ዳር ተቀምጦ ወደ ዛፉ ሲመለከት አንድ ትል የዛፏን ፍሬ ለመመገብ ፈልጎ ወደ ላይ እየወጣና እየወደቀ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በሰባተኛው ጊዜ ወደ ዛፉ ወጥቶ ፍሬዋን ሲመገብ ተመለከተ  ተማሪ ያሬድም ከዚህ ትል ትዕግሥትን፣ ጽናትን፣ ጥረትን፣ ስኬትን ትምህርት ወስዶ እኔም እኮ ተስፋ ሳልቆርጥ ብዙ ጥረት ካደረግኹ እግዚአብሔር ያሳካልኛል ብሎ በተስፋ ተጽናንቶ እንደገና ወደ መምህሩ በመመለስ ትምህርቱን ለመቀጠል ወሰነ፡፡



**ማይኪራህ - ቅዱስ ያሬድ ትዕግሥትና ጽናትን የተማረባት ቦታ**

የአጎቱ ምክርና ተግሣጽ ለሕይወቱ የሚጠቅም እንደኾነ በመረዳት ትምህርቱን በትጋት ቢማርና ቢያጠና ያሰበው ደረጃ መድረስ እንደሚችል በመገንዘብ ወደ መደባይ ያደርገው የነበረውን ጉዞ ሠርዞ ወደ አክሱም ከተማ ወደ መምህሩ ጌዴዎን ጉባኤ ቤት ተመለሰ፡፡ ቀድሞ በፈጸመው የብስጭት ተግባር በመጸጸት አጎቱን “አባቴ ስለተቆጣኸኝና ስለገረፍከኝ ተበሳጭቼ ሄጄ ነበር፤ ነገር ግን በመንገድ ላይ እግዚአብሔር ስላስተማረኝ ተጸጽቼ መጥቻለኹ፡፡  ከእንግዲህስ ወዲህ እየተቆጣኸና እየገሠጽህ አስተምረኝ” ሲል አሳቡን ሳይደብቅ ገለጸለት፡፡

አጎቱም ያሬድ ተጸጽቶ በመመለሱ በጣም ተደሰተ፡፡ ቅዱስ ያሬድም  ዐይነ ልቡናውን ያበራለት ዘንድ  ፈጣሪውን እያለቀሰ በለመነ ጊዜ እግዚአብሔርም  ጸሎቱን ሰምቶ  ዕውቀትን ገለጸለት፡፡ “ተርኅወ ኅሊናሁ፤ የያሬድ ኅሊናው ተከፈተ ማለት

ልቡናው ብሩሕ ኾነ፡፡ ቅዱስ ያሬድም  መዝሙረ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምን፣ መሐልየ ነቢያትን፣ መሐልየ ሰሎሞንን፣ መጻሕፍተ ብሉያትንና መጻሕፍተ ሐዲሳትን ንባባቸውን እስከ አገባባቸው ዐወቀ፡፡ መምህሩ ጌዴዎንም ጸጋ እግዚአብሔር እንዳደረበትና መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸለት ለማወቅ መዝሙረ ዳዊትን ቢፈትነው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዘልቆታል፡፡

የቀድሞ ኹኔታውንና የኋላውን አያያዙን ያዩ የመምህሩ ጌዴዎን ደቀ መዛሙርት፣ በዘመኑ የነበሩ የአክሱም ጽዮን ካህናትና በአካባቢው የሚኖሩ ሊቃውንት ሁሉ ነገሩ ስለደነቃቸው “ያሬድኑ እም ውስተ ነቢያት ወሚመ እመላእክት፤ የያሬድ ቁጥሩ ከነቢያት ነው፣ ወይንስ ከመላእክት? ሌላ ሰው ኾነብንሳ!” ይሉ ነበር፡፡ ሰው መሆኑ ተለወጠ ማለታቸው አይደለም፤ ባለአዕምሮ የዕውቀት ባለቤት ሆነ ሲሉ ነው እንጂ፤ ምድራዊ ሰው ሲኾን ሰማያዊ መልአክ ሆኖባቸዋልና፡፡  ከእርሱ በኋላ የተነሡ ሊቃውንትም የመጀመሪያ ትምህርቱን ጠቅሰው፡-

ካህን ያሬድ እንተ ትገብር መንክረ
እም ንኡስ ዕፄ ነጺረከ ምግባረ
ወበእንተዝ ተመየጥከ ትትመሀር መዝሙረ

(ብዙ ትምህርት ተአምራት ያደረግኽ ካህን ያሬድ ሆይ፣ ከትንሿ ትል ኀይልን፣ ብርታትን፣ ጽናትን ተመልክተኽ መዝሙርን ትማር ዘንድ ወደድኽ) ብለው ጽፈውለታል፡፡ በተጨማሪም፤

ሰላም ለያሬድ ስብሐተ መላእክት ለሕዋጼ
እንተ አዕረገ በልቡ ኀሊና መንፈስ ረዋጼ
ለትምህርተ መጽሐፍ ገብአ እም ኀበ ኮነ ነፋጼ
በብዙኀ ፃማ ዘአልቦ ሑጻጼ
መልዕልተ  ጒንደ ዕፅ ነጺሮ እንዘ የዓርግ ዕጼ

ትርጓሜውም፡- “የመላእክትን ምስጋና ለመጎብኘት ፈጣን የመንፈስ ኀሊናን በልቡናው ላሳደረ ለያሬድ ሰላምታ ይገባል፡፡ ጉድለት በሌለበት በብዙ ድካም ትል ወደ ዛፍ ሲወጣ አይቶ ከሸሸ በኋላ መጻሕፍትን ለመማር ተመልሷልና” የሚል አርኬ ጽፈውለታል፡፡ ይህንኑ አርኬ የዜማ መምህራን ጧት ጉባኤያቸውን በሚዘረጉበት ጊዜ ጸሎት አድርገው ያደርሱታል፤ ተማሪዎቻቸውንም ያስደርሷቸዋል፡፡ ይኸውም የአባታቸውን የቅዱስ ያሬድን በረከት ለመሳተፍ መፈለጋቸውን ያሳያል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቃሉ ይዞ ሲያስተምር ሳለ የትምህርቱን ጥራት፣ የሃይማኖቱን ጽናት፣ ደግነቱና ትዕግሥቱ፣ ትሕትናውና ተልእኮው በመምህሩ እና በካህናቱ ተመስክሮለት የአክሱም ጳጳስ አባ ዮሐንስ ሢመተ ዲቁና ሾመው፡፡ ቅዱስ ያሬድ የታላቋ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ዲያቆን ኾነ፡፡ ትምህርቱን በስፋት ስለቀጠለበት የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሐዲሳት እና የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ ሊቅ ኾነ፡፡ ቅዱስ ያሬድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ከዘጠኙ ቅዱሳን ጋራ በቤተ ቀጢን (ጉባኤ ቤት)  ይውል ስለነበር ገዳማዊ ሕይወትን ከእነርሱ በመማር እንደ እነ አባ ገሪማ፣ አባ ጰንጠሌዎን፣  በድንግልና ተወስኖ በንጽሕና ሲያገለግል  ቆይቷል፡፡

እግዚአብሔር አንድ ትልቅ ሥራ ለመሥራት በፈለገ ጊዜ ለሥራው መገለጫ በሆኑ ሰዎች ላይ መጠነኛ የሆነ ፈተና ያሳያል፡፡ ይኸውም ለእናታችን ሣራ ደጉን ይሥሐቅን፣ ለቅድስት ኤልሳቤጥ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን፣ ለቅድስት ሐናም ድንግል ማርያምን የሚያህሉ ልጆችን ለመስጠት በፈለገ ጊዜ በመጀመሪያ በመካንነት ብዙ ጊዜ እንዲቆዩ አድርጓል፡፡ የኋላ ኋላ ግን ሙቀት ልምላሜና አበባ ቢለያቸውም በከሃሊነቱ ወልደው እንዲታቀፉ አድርጓቸዋል፡፡ ዘፍ. 18፡10-40፤ 1ኛ ሳሙ. 1፡2-8፤ ሉቃ.1፡7 ዓይነ ሥውር ኾኖ የተወለደው ሰውም ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ዓይነ ሥውር ኾኖ እንዲወለድ ካደረገ በኋላ በከሃሊነቱ ብርሃነ ዐይን ሰጥቶታል፡፡ ይህም ለምን ዐይነ ሥውር ኾኖ እንደተወለደ በደቀ መዛሙርቱ ለቀረበለት ጥያቄ ጌታችን ሲመልስ "የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው" ሲል ገልጿል፡፡ ዮሐ. 9፡1-4፡፡ እንደዚሁም ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ትምህርት አልገባ ብሎት ለብዙ ጊዜ መጉላላት ነሺም፣ ሰጭም፣ ገላጭም እግዚአብሔር መኾኑን ለመግለጽ የተጠቀመበት ኹኔታ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ ቅዱስ ያሬድ ከመጀመሪያ ጀምሮ በጣም ዐዋቂና ትምህርት ተቀባይ ተማሪ ቢኾን ኖሮ ሰዎች የተገለጸለትን ዜማም ካለው የቆየ ዕውቀት እንደተገኘ አድርገው ይገምቱ ነበር፤ ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር የመቀበል ችሎታው ደካማ የነበረው ቅዱስ ያሬድ እንደገና እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከፍተኛ ሊቅና የዜማ ደራሲ ኾኖ መገኘቱ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትና ሁሉን ሰጭነት በተጨባጭ የሚያስረዳና የቅዱስ ያሬድ ዜማም በሥጋዊ ዕውቀት የተገኘ ሳይኾን በእግዚአብሔር ገላጭነት መገኘቱን የሚገልጽ ነው፡፡

**ለቅዱስ ያሬድ ሰማያዊ ዜማ መገለጽ**

ዐፄ ገብረ መስቀል በአባታቸው በዓፄ ካሌብ ተተክተው በነገሡበት ዘመን ቅዱስ ያሬድን የወደደ፣ ሀገሪቷን ኢትዮጵያንም የመረጠ እግዚአብሔር ለመረጠው ለቅዱስ ያሬድ የዘለዓለም መታሰቢያ እንዲቆምለትና ሀገሩ ኢትዮጵያም በሚያስተምራት ማኅሌተ መላእክት እያመሰገነችው፣ እያከበረችው እንድትኖር ቅዱስ ፈቃዱ ስለሆነ ኅዳር 5 ቀን 5፻፷7 ዓ.ም ከጠዋቱ በሦስት ሰዓት (በሠለስት) ከኤዶም ገነት ሦስት አዕዋፍን (መላእክት በአዕዋፍ ተመስለው) እርሱ ወዳለበት ላከለት፡፡ እነርሱም ያሬድ ባለበት ቦታ አንጻር በአየር ላይ ረብበው በግእዝ ቋንቋ "ብፁዕ ያሬድ ብፅዕት ከርሥ እንተ ጾረተከ ወብፁዕት አጥባት እለ ሐፀናከ፣ የተመሰገንክና የተከበርክ ያሬድ ሆይ፥ አንተን የተሸከመች ማሕፀን የተመሰገነች ናት፤ አንተን ያሳደጉ ጡቶችም የተመሰገኑ ናቸው" ብለው አወደሱት፡፡ ቅዱስ ያሬድም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ወደ ሰማይ አንጋጦ ሦስቱን አዕዋፍ አየና "እናንተ በሰው አንደበት የምትናገሩ ከወዴት መጣችኹ" አላቸው፡፡ ከሦስቱ አዕዋፍ አንዷም "ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ማኅሌትን ሰምተኽ እንድታዜም የተመረጥኽ መኾኑን እንነግርህና እናበሥርህ ዘንድ ወደ አንተ ተልከን መጥተናል" አለችው፡፡ ከዚያም ቅዱሳን መላእክት በዜማ ወደሚያመሰግኑባት ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም በአካል ተነጠቀ፡፡

በዚያም ቅዱሳን መላእክት የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ እግዚአብሔርን በቅኔና በከፍተኛ ደምፅ ያለማቋረጥ በመንበሩ ዙሪያ ኾነው ሲያመሰግኑ እንዲሁም የእንዚራ፣ የበገና የመሰንቆ ድምፅ በሰማ ጊዜ ካለበት ሥፍራ እነርሱ ወዳሉበት ሊገባ ወደደ ነገር ግን አልተቻለውም፡፡ በመጨረሻም እነዚያ አዕዋፍ ወደ እርሱ ተመልሰው መጡ፡፡ "ያሬድ ሆይ፤ የሰማኸውን አስተውለኸዋል?" ብለው ጠየቁት፡፡ "አላስተዋልኹም" ብሎ መለሰላቸው፡፡ "እንግዲያውስ አዲሱን የእግዚአብሔርን ምስጋና ጥራ፤ እርሱም የጌታችን የመድኅኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፡፡ ከእግዚአብሔር መዘምራን ከቅዱሳን መላእክት በየዐይነቱ ዜማ ያለውን ማኅሌት ትማራለኽ፤ ታጠናለኽ" አሉት፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ያሬድ ማኅሌቱን በየዐይነቱ አውጥቶ

“መልካምን ነገር ልቤ ተናገረ” እያለ ከቅዱሳን መላእክት ተማረ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም “ሌሎችን አገልጋዮች ሰዎች ይሾሟቸዋል፤ አንተን ግን እኔ ሢመተ ክህነት (ቅስና) ሾሜኻለሁ” አለው፡፡

ቅዱስ ያሬድም ከጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሢመተ ክህነትን ተሹሞ፣ የመላእክት ሥርዐታቸውን ዐይቶ፣ ማኅሌታቸውን አጥንቶ ኅዳር 6 ቀን 5፻፳7 ዓ.ም በጠዋት ሦስት ሰዓት ወደ ቀድሞ ቦታው ተመልሷል፡፡ ከዚያም ኾኖ ፊቱን ታቦተ ጽዮን ወዳለችበት ወደ ምሥራቅ አዞሮ፥ እጆቹን ዘርግቶ እንዲህ ብሎ ሰማያዊ ዜማውን ለመጀመሪያ ጊዜ በአኲሱም አደባባይ (ዐውደ ምሕረት) ዘመረ ፡፡

ሃሌ ሉያ ለአብ፣ ሃሌ ሉያ ለወልድ፣ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ

ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ

ብሎ በዓራራይ ዜማ አዜመ፡፡ (አርያም፣ጾመ ድጓ) ይህም ማለት ዓለም ሳይፈጠር ለነበረና ዓለምን አሳልፎ ለዘለዓለም ለሚኖር ለአብ ምስጋና ይገባል፤ ለወልድም ምስጋና ይገባል፤ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል፤ ከጽዮን አስቀድሞ ሰማይን ፈጠረ፤ ዳግመኛም ደብተራ ኦሪትን እንዴት አድርጎ መሥራት እንዳለበት ለሙሴ አሳየው ማለት ነው፡፡ ኦሪት ዘፀ. ፳5፥8-0 ፤ ፳6፥፴፡፡ ስለምን በዓራራይ ጀመረ ቢሉ ቋንቋን የሚያናግር ምስጢር የሚያስተረጉም መንፈስ ቅዱስ የገለጠልኝ ዜማ ነው ሲል ነው፡፡ ምክንያቱም ዓራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነውና፡፡

ከሰማይ እንደተመለሰ ለመጀመሪያ ጊዜ ጣዕመ ዜማውን ያሰማበት ቦታ ”ሙራደ ቃል” (የቃል መውረጃ) እየተባለ ይጠራል፡፡ ይኸውም ዜማው ከሰማይ የወረደ ለመኾኑ እውነተኛ ማስረጃ ነው፡፡ ይህችንም ዜማ ”አርያም” አላት፡፡ ይህም ማለት ከመላእክት ወይም ከሰማይ የተገኘች ማለት ነው፡፡ እርሷም ሳትጠፋ ለዘለዓለም ትኖራለች ፡፡



**ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያውን ዜማ ያዜመባት ሙራደ ቃል**

ከዚህም በተጨማሪ ዜማውን በመንበረ ጸባኦት ዙሪያ ኾነው እግዚአብሔርን ከሚያመሰግኑ ከቅዱሳን መላእክት የሰማው መኾኑን ራሱ ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ሲል ገልጾታል "ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን እንዘ ይብሉ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር መልአ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ፣(ዋዜማ፣ድጓ) ከቅዱሳን መላእክት በሰማይ የሰማኹት ዜማ ዋ! ምን ይደንቅ! ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ፥ የክብርኽ ምስጋና ሰማያትንና ምድርን መላ እያሉ" ሲል ድጓ በተባለው ድርሰቱ ገልጾታል፡፡ እንዲሁም ዝማሬ በተባለው ድርሰቱ

ሰማየ በአብ ወበወልድ አርያመ ወበመንፈስ ቅዱስ ኀበ ዐረጉ
ሰማዕኩ እመላእክት ዝማሬ በአድንኖ ወበአትሕቶ ቦ ዘያጽሕሱ ወቦ ዘይዜምሩ (ዝማሬ)

ትርጓሜውም በአብ ወደ ሰማይ በወልድ ወደ አርያም በመንፈስ ቅዱስም በወጣሁ ጊዜ ከመላእክት ዘንድ ዝማሬን ሰማኹ የሚያሸበሽቡም አሉ፤ የሚዘምሩም አሉ) ማለት ነው፡፡

የቅዱስ ያሬድ ወደ ሰማይ መነጠቅና ከዚያም የመላእክትን ዝማሬ ሰምቶ መመለስ ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ መነጠቅና ከቅዱስ ያሬድ በኋላ ከተጠሩት ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ሰማይ ተነጥቀው ከኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ መላእክት ጋር ኾነው የሥላሴን መንበር በማጠን አብረው ካመሰገኑት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛው መልእክቱ ስላየው ሰማያዊ ራእይ ሲገልጽ "እንዲህ ያለው ሰው ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፤ . . . ወደ ገነት ተነጠቀ ሰውም ሊናገረው የማይገባውንና የማይናገረውን ቃል ሰማ" 2ኛ ቆሮ. 12፡1-5 ብሏል፡፡

ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተጠሩት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል ላይ ተመዝግቦ የምናገኘውም እንዲህ ይላል "ይህቺ ታላቅ ጸጋ ክብር ትሰጠኝ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ አልኩት እግዚአብሔርም ለወደደው ባለሟልነቱንና ክብርን ይሰጣልና ነው አለኝ፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ሰማይ አውጥቶ ከመጋረጃ ውስጥ አግብቶ ከሥላሴ ዙፋን ፊት ለፊት አቆመኝ:: ተክለ ሃይማኖት ክፍልህ ከኻያ አራቱ ካህናቶቼ ጋር ይሁን የሚል ቃል ከዙፋኑ ውስጥ ወጣ፡፡ የወርቅ ጽና አምጥተው እሷን ሰጡኝና ከእነሱ ጋር አንድነት አጠንኩ ምስጋናዬ እንደምስጋናቸው ልብሴም እንደልብሳቸው ሆነ፡፡ ፈጣሪዬንም በሦስትነቱ ተገልጾ አየሁት፡፡" (ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘዐርብ ምዕራፍ. 46፡28-29) በእግዚአብሔር ዘንድ ለትልቅ ነገር የተመረጡ ሰዎች ወደ ሰማይ እየተነጠቁ መወሰድና በዚያም ልዩ የኾነ ራእይ ማየት የተለመደ መኾኑን የቅዱስ ጳውሎስና የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አነጋገር ያረጋግጥልናል፡፡ ቅዱስ ያሬድም እንደ ቅዱስ ጳውሎስና እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ሰማይ መነጠቁ ከድሮም ጀምሮ የተለመደ የእግዚአብሔር አሠራር እንጂ አዲስ ነገር እንዳልኾነ በዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ማሰማት የጀመረበት ቀን ኅዳር 6 ቀን ስለነበር መሐሪው እግዚአብሔር በሕፃንነቴ ጊዜ የነበረኝን የትምህርት አለመቀበል ችግር አስወግዶ ለዚህ አበቃኝ ሲል "አስተምህሮ" ብሎ ወቅቱን ሰየመው፡፡ በዚህ ቀን ቅዱስ ያሬድ በሙራደ ቃል ኾኖ የዜማ ድምፁን ከፍ አድርጎ ባሰማ ጊዜ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተቃኘው ድምፁ ከቃናው ጣዕም የተነሣ እጅግ ልብን የሚመስጥና የሚያስደስት በመኾኑ ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል፣ ንግሥቲቱ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ሊቃውንቱና

ካህናቱ፣ እንስሳና አዕዋፍ ሁሉ “አዲስ ነገር ተገኝቷልና እንሂድ” እየተባባሉ እርሱ ወዳለበት ቦታ ተሰብስበው ከጣዕሙ የተነሣ መንፈስን የሚያድሰውን፣ ልቡናን የሚያስደስተውንና አጥንትን የሚያለመልመውን አዲሱን ሰማያዊ ዜማ ረሀብና ጥም ሳይሰማቸው በከፍተኛ ተመስጦ እና አድናቆት ሲሰሙ ዋሉ ፡፡

ቅዱስ ያሬድ በግእዝ፣ በዕዝልና በዓራራይ ዜማውን እያስማማ እግዚአብሔርን ማመስገኑን ቀጠለ፡፡ ዐፄ ገብረ መስቀል የዜማውን ጣዕም ከሰሙና ከተረዱ በኋላ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መገልገያና ለሕዝቡ መባረኪያ የሰጣቸው መኾኑን በመገንዘብ ሊቃውንቱንና ካህናቱን “ተቀበሉትና ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ ይኹን” ብለው አዘዟቸው፤ ነገር ግን ካህናቱና ሊቃውንቱ “ምን ምልክት ዐይተን እንቀበለው፤ እንደ ሐዋርያት እጁንና እግሩን ለተሳለ ቀኖት (ችንካር)፣ አፉን ለምረረ ሐሞት ሰጥቶ አላየነው፤” ብለው መለሱላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ንጉሡ “እንግዲያውስ ሱባዔ እንያዝና እርሱ አምላካችን እግዚአብሔር ይግለጽልን” ብለው ከታኅሣሥ አንድ ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ሰባት ቀን ሱባዔ እንዲያዝ ዐወጁ ፡፡

በዚያን ጊዜ ታኅሣሥ አንድ ቀን ሰኞ ዕለት ውሎ ነበርና ከሰኞ እሰከ እሑድ አንድ ሱባዔ ይዘው በየቀኑ የአኲሱም ጽዮን ማርያምን ቤተ ክርስቲያን እየዞሩ አራት መቶ እግዚኦታና አርባ አንድ በእንተ ማርያም እያደረሱ ምሕላውን አካሄዱ፡፡



**በቅርብ ጊዜ በሙራደ ቃል ካህናትና ምእመናን ጸሎተ ምሕላ ሲያካሒዱ**

በሰባተኛው ቀን እሑድ ዕለተ ምህላውን ጨርሰው ሲያሳርጉ ጌታ በዕለተ ዐርብ እንደተሰቀለ ኾኖ በአኲሱም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ተገለጸ፡፡ ከዚህም አያይዞ ቅዱስ ያሬድ “ዘበመስቀሉ ተቀነወ ወበነቢያት ተሰብከ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ሰብሕዎ ኪያሁ ንሰብክ መድኅነ” (ስብከት፣ድጓ) ብሎ ነገረ መስቀሉን በማውሳት የወልድ ምሳሌ በኾነው በዕዝል ዜማ ዘመረ፡፡ ትርጓሜውም፥ “በነቢያት ትንቢት የተነገረለትና በመስቀሉ ላይ የተቸነከረው ጌታ መላእክትና የመላእክት አለቆች አመሰገኑት፤ እኛም እርሱ መድኀኒት እንደሆነ እንናገራለን፤” ማለት ነው፡፡ ይህም ቀን ስብከት ተብሎ ተሰየመ፡፡

ስብከት መባሉም ቅዱስ ያሬድ ዜማ ማስተማር የጀመረበት ነቢያት ይወርዳል፣ ይወለዳል ብለው የተናገሩት ትንቢት ለመፈጸሙ መታሰቢያ ስለኾነ ነው፤ ዘበመስቀሉ ተቀነወ ማለቱ መውረዱ፣ መወለዱ፣ ተሰቅሎ መሞቱ ዓለምን ለማዳን ነውና፡፡ በዚህ በተገለጸው ምስክርነት መሠረት ዜማው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ መኾኑን አምነው ቤተ መንግሥቱ፣ ቤተ ክህነቱ እና ሕዝቡ በአንድነት ተቀበሉት፡፡ በዚህም ቀን ቅዱስ ያሬድ ከሰማይ የተቀበለው ዜማ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ብርሃኗ በራ በሰማያዊ ምስጋና ቤተ መቅደሱ መላ፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያሬድን በእልልታ ተቀበለችው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ስሙ እንደሚያመለክተው ሰማያዊ ዜማን ወደ ምድር አወረደ፤ ስም በተግባር ተገለጸ፤ "የመላእክት እንጀራን የሰው ልጅ በላ፤ ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠኻቸው" የተባለው የቅዱስ ዳዊት የትንቢት ቃል ተፈጸመ፡፡ በዚህ ጊዜ "ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሴብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን" ያለው የወንጌል ቃል ተፈጸመ፤ ትርጉሙም መላእክትና የሰው ልጆች በሃይማኖት ቃል እግዚአብሔር ክርስቶስን ያመሰግኑ ዘንድ አንድ ጉባኤ ኾኑ ማለት ነው፡፡ በዚህም "የአዳም ምስጋና ከመላእክት ምስጋና ጋራ አንድ ሆነ ምስጋናቸውም የተስተካከለ ሆነ" ተብሎ የተነገረው ቃል ተረጋገጠ፡፡ 3ኛ መቃብያን. 4፥01 ከዚህች ዕለት (ታኅሣሥ ሰባት ቀን 527 ዓ.ም) ጀምሮ የቅዱስ ያሬድ ዜማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መደበኛ መገልገያ ኾነ፡፡ ቅዳሴው በቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ተቀነባበረ፡፡ የአኩሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ዜማ ከዓመት እስከ ዓመት ያለማቋረጥ የሚዘመርባት በምድር ያለች ሁለተኛ ጽርሐ አርያም ኾነች:: የአኩሱም ጽዮን ደባትር፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ወደ ቅዱስ ያሬድ ጉባኤ ቤት (ቤተ ቀጢን) ገብተው ዜማውን በትጋትና በንቃት ይማሩ ጀመር፡፡

በቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ እጅግ ተመስጦ የነበራቸውና በማንኛውም መልኩ ዜማው እንዲስፋፋ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ የነበሩት ንጉሡ ነገሥቱ ዐፄ ገብረ መስቀልም ለቅዱስ ያሬድ ደቀ መዛሙርት ሰፊ ድጋፍ ያደርጉ ነበር፡፡ ይህንም የቅዱስ ያሬድ መጽሐፈ ገድል እንዲህ ብሎ ይገልጸዋል፡፡ "ወአንበሮሙ በዐቢይ ክብር ንጉሥ ገብረ መስቀል ለመምህር ወለረድኡ ወይሁቦሙ ሲሳዮሙ በበጊዜሁ ዘይሤኒ ወመስቴሂ ወይነ ዘያስተፌሥሕ ልቦሙ ይሁቦሙ በበጊዜሁ ወያለብሶሙ ልብሰ ሜላት ወአልባሰ ወርቅ፤ ንጉሥ ገብረ መስቀል መምህሩንና ደቀመዛሙርቱን በታላቅ ክብር አስቀመጣቸው፤ እንደዚሁም ያማረ ምግብና የሚያስደስት የወይን መጠጥን በየጊዜው ይሰጣቸው ነበር፤ የሐር የወርቅ ልብስም ያለብሳቸው ነበር" ማለት ነው፡፡

የቅዱስ ያሬድ ዜማ በፈቃደ እግዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸ ለመኾኑ ማስረጃው ለአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ጸንቶ መኖሩ፣ ሳይለወጥ እየበረታ እየሰፋ መሄዱ፣ ብዙ ሊቃውንት የእርሱን ፈለግ ተከትለው ጊዜያቸውንና መላ ዘመናቸውን መሥዋዕት በማድረግ በዚሁ ማሳለፋቸው ይልቁንም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ በማያቋርጥ ኹኔታ ድምጿ አድርጋው መኖሯ ታላቅ ማስረጃ ነው፡፡

**የቅዱስ ያሬድ ሐዋርያዊ አገልግሎት**

ሐዋርያ የሚለው ቃል ሖረ፣ ሄደ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ነው፤ ትርጓሜም የሚሄድ፣ የሚዘዋወር ሰባኪ፣ አስተማሪ፣ ተላኪ ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያን በተለያዩ ቦታዎች ዞሮ በማስተማሩ፣ ከእግዚአብሔር ተልኮ ሰማያዊውን የመላእክት ዜማ በማስተማሩ፣ የእግዚአብሔርን አምላክነት፣የእመቤታችንን ክብር ከመመስከሩ በተጨማሪ የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን፣ የመላእክትን ክብራቸውን በመግለጽ መስክሯልና ምስክር ይባላል፡፡ ቅዱስ


ያሬድ በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር የተለያዩ ሐዋርያዊ አገልግቶችን አከናውኗል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ፡፡

ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ለሥርዐተ ምንኲስና አገልግሎት የሚሆንና ከከተማ ወጣ ያለ ምቹ ቦታ ሲፈልጉ ከአክሱም ከተማ ወደ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ለዚሁ አገልግሎት የሚሆን የደብረ ዳሞ ተራራን አገኙ፡፡ የተራራውን አቀማመጥ ዐይተው ደስ ስላላቸው ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል በዚህ ተራራ ላይ እንዲኖሩበትና እንዲጸልዩበት ፈቀደላቸው፡፡ አቡነ አረጋዊ በተራራው ላይ የጸሎት ቤት ስለሌለ ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል አንድ ቤት ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ለመኑት፤ ንጉሡም ቤተ ክርስቲያን ሠራላቸው፡፡ አቡነ አረጋዊም ቤተ ክርስቲያኑን ባርከው የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ታቦት አስገብተው ቅዳሴ ቤቱ ከተከናወነ በኋላ ቅዱስ ያሬድ የሚያስተምረው አክሱም ስለነበር መጥቶ እንዲጎበኝላቸው መንፈሳዊ ጥሪ አደረጉለት፡፡

እርሱም ከአክሱም ተነሥቶ መጥቶ ከተራራው ሥር ሲደርስ የአቡነ አረጋዊን ደቀ መዛሙርት ማትያስንና ዮሴፍን አግኝቶ “ዳኅንኑ ዝስኩ አረጋዊ አቡክሙ፤ ይህ አረጋዊ አባታችሁ ደኅና ነውን?” ብሎ በዓራራይ ዜማ እያዜመ ቢጠይቃቸው እነርሱም ተደንቀው ለአቡነ አረጋዊ ለመንገር ወደ ተራራው ገሠገሡ፡፡ አቡነ አረጋዊም ሳይነገራቸው በጺጋ ዐውቀው ተማሪዎቻቸውን “ንዑ ንሑር ኀበ ያሬድ ካህን እንዚራሃ ለቤተ ክርስቲያን” ብለው ወርደው ቅዱስ ያሬድን አግኝተው በመንፈሳዊ አምኃ በፍቅር ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ ቅዱስ ያሬድም ወደ ቤተ ክርስቲያኗ በወጣ ጊዜ ሦስት ጊዜ ሰግዶ ከተሳለመ በኋላ የሕንፃውን ማማር በአድናቆት ተመልክቶ ቤተ ክርስቲያኗን የሚጠብቁ መላእክት የእሳት ሰይፍ ይዘው ቢታዩት ከፍ ባለ የዜማ ድምፅ እንዲህ ሲል ዘመረ፡፡ “ይሔውጽዋ መላእክት እንተ በሰማያት ይሔውጽዋ መላእክት እስመ ማኅደረ መለኮት ይእቲ ዖድክዋ፣ ዖድክዋ፣ዖድክዋ ወርኢኩ ሥነ ሕንፄሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምስአል ወምስጋድ ወምስትስራዬ ኀጢአት ይእቲ ቅድስት ደብተራ፤ (አስተምሕሮ፣ድጓ) በሰማያት ያሉ መላእክት ይጎበኟታል፤ የመለኮት ማደሪያ ናትና መላእክት ይጎበኟታል፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዞርኋት፣ ዞርኋት፣ ዞርኋት የሕንፃዋን ማማርም ዐየኹ፤ እርሷ መጸለያ፣ መስገጃና የኀጢአት ማስተስረያ ቅድስት ማደሪያ ናትና” እያለ ስለዘመረ ደብረ ሃሌ ሉያ ተብሎ ተጠራ፡፡ ደብረ ዳሞ የሚለው ስያሜ በኋላ የወጣ ስም እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡

ቅዱስ ያሬድ በዚሁ ገዳም ስምንት ቀናት ያህል ከአቡነ አረጋዊ ጋር ቆይቶ ወደ አክሱም ተመለሰ፡፡


ንጉሡ ዓፄ ገብረ መስቀል፣ አቡነ አረጋዊ እና ቅዱስ ያሬድ ከአኩሱም ተነሥተው በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመጓዝ ጣና ሐይቅ ደረሱ፡፡ በጣና ሐይቅ ውስጥ ጣና ቂርቆስ እየተባለ በሚጠራው ደሴት ላይ ብዙ ቀናትን አሳለፉ፡፡ በዚህ ቦታ ቅዱስ ያሬድ ለሁለት ዓመታት አስተማረ፡፡ እርሱ ራሱ የጻፈው ምልክት የሌለው ድጓና ቀለም ይበጠብጥበት የነበረው የቀለም መበጥበጫ ሙሣሪያ እስከ ዛሬ ድረስ በጣና ቂርቆስ ገዳም ይገኛል፡፡ እንዲሁም የቅዱስ ያሬድና የዓፄ ገብረ መስቀል እግራቸው እንደ አንካሴ የሾለና በመስቀል ቅርጽ የተቀረጹ መቋሚያዎች፣ የሁለቱም ካባዎች በዚህ ገዳም ውስጥ ይገኛሉ፡፡



ቅዱስ ያሬድ የጻፈው ምልክት የሌለው ድጓ በጣና ቂርቆስ ገዳም



ቅዱስ ያሬድ ድጓውን ሲጽፍ ቀለም ይበጠብጥበት የነበረ
ከድንጋይ የተሠራ ቀለም መበጥበጫ በጣና ቂርቆስ ገዳም



**የቅዱስ ያሬድ ካባ በጣና ቂርቆስ ገዳም**



**መስቀለ ያሬድ በጣና ቂርቆስ ገዳም**

ከዚህ በኋላ ንጉሡ፣ አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ያሬድ ከጣና ቂርቆስ ተነሥተው ወደ ደጋው ወደ ጋይንት ወጡ፡፡ በዚያም አንድ ትልቅ ተራራ አግኝተው መውጫው ጠፍቶባቸው በሱባዔ ላይ እያሉ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ተገልጾ “ዑድ አባ መንገለ ምሥራቅ ወዑዳ ለዛቲ ደብር፤ ዙር አባ ወደ እርስዋም ትወጣ ዘንድ በምሥራቅ በኩል ዙር” አላቸውና ወደ ምሥራቅ ሲዞሩ መልአኩ ዑራኤል ነጭ ሐረግ ዘረጋላቸውና እርሱን ይዘው ወደ ተራራው ጫፍ ወጡ፡፡



***መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ነጭ ሐረግ ዘርግቶላቸው አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ያሬድ***
***ሐረጉን ይዘው ወደ ተራራው ጫፍ ላይ ሲወጡ***

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ ዙር አምባ (ዙር አባ) በመባል ይታወቃል፡፡ አቡነ አረጋዊ ቦታውን ተመልክተው ስለወደዱት በቦታው ገዳም ለመትከል አሰቡ፡፡ ዐፄ ገብረ መስቀልን አስፈቅደው የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም አሠሩ፡፡


በዚህ ገዳም ምሥራቃዊ አቅጣጫ ቅዱስ ያሬድን የምትዘክር "ከርሞ አይደርቅ"የምትባል ዛፍ አለች፡፡



**ከርሞ አይደርቅ ዛፍ *ዙር አምባ አቡነ አረጋዊ ገዳም***

ቅዱስ ያሬድ በዚች ዛፍ ሥር ተቀምጦ ዝማሬ መዋሥዕትን ለሦስት ዓመት ከሦስት ወር ስላስተማረባት ገዳሟ የዝማሬ መዋሥዕት ማስመስከሪያ ቦታ ኾናለች፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር በገለጸበት ጊዜ በሥጋ ከሞተ ብዙ ጊዜ የሆነውን ሙሴን በአካለ ነፍስ አምጥቶ ብርሃነ መለኮቱን እንዲመለከት እንዳደረገ ሁሉ  ቅዱስ ያሬድም ከአኵሱም ወደ ማይኪራህ አምርቶ እመቤታችን ቅዱስ ኤፍሬምን በአካለ ነፍስ ከሶርያ አባ ሕርቆስን ከብሕንሳ አምጥታ ውዳሴዋንና ቅዳሴዋን ንባቡን እየነገሩት በዜማ እንዲደርስላት አድርጋለች ፡፡ ከዚህም አያይዞ ለሥጋ ወደሙ ጸሎት የሚያገለግሉትን ንባባቸው የሌሎች ሊቃውንት ድርሰት የሆኑትን የተቀኙትን ቅዳሴዎች በዜማ አዘጋጀ፡፡



**ቅዱስ ኤፍሬምንና አባ ሕርቆስን  ውዳሴዋንና ቅዳሴዋን ንባቡን እየነገሩት ቅዱስ ያሬድ  ዜማ ሲደርስ በማይኪራህ**

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ያሬድ ወደ ስሜን ተራሮች ጸለምት ሄዶ ምዕራፍ የተባለውን ድርሰቱን ደረሰ፡፡ ከዚህ በኋላ አገው፣ ፎገራ እና ወደ ሌሎችም ቦታዎች እየዞረ አስተማረ፡፡

***ወርቀ ደም***

ቅዱስ ያሬድ ዜማውን በሚያዜምበት ጊዜ ጣዕመ ዜማውን ሲሰሙ አዕዋፍ በሰማይ ክንፋቸውን ረበው ሲዳዙ በመሬት እንስሳት አራዊት ይከተሉት ነበር፡፡ የተጠመዱ በሬዎች እንኳን ሳይቀሩ ዜማውን ያዳምጡ ነበር ፡፡ በጎንደር ክፍለ ሀገር ወገራ አውራጃ በአምባ ጊዮርጊስ ወረዳ ልዩ ስሙ ሰርዶ ሜዳ በሚባል ቦታ ቅዱስ ያሬድ “ዘሪ ሊዘራ ወጣ ሲዘራም አንዳንዱ ቅንጣት ባልሆነ ስፍራ ወደቀ” ማቴ. 03 ተብሎ በምሳሌ ዘር የተነገረውን በዜማው አግብቶ ቃሉን ከፍ አድርጎ  እያዜመ በሚሔድበት ጊዜ ተጠምደው በእርሻ ላይ ያሉ በሬዎች እያዳመጡ አልንቀሳቀስም ስላሉ ገበሬዎች ተሰብስበው ቅዱስ ያሬድን፡- “አንተ ሥራ ፈት ተማሪ ፤ራስህ ሥራ ፈተኽ ሌላውን ሥራ ታስፈታለኽ” በማለት  ገርፈውታል፡፡ ለዚያም ነው ‘ወገረ’ ከሚለው የግዕዝ ቃል ወገራ የሚል ስያሜ መጥቶ የአካባቢው መጠሪያ የሆነው” ቦታውም “ወርቀ ደም” እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ ይጠራል ፡፡ ወርቃማ ደሙ የፈሰሰበት ማለት ነው ቅዱስ ያሬድ በወገራ ምድር ላይ በአርሶ አደሮች በመገረፉ አካባቢውን አይጥ እንዲወርረው፣ በቂ ምርት እንዳያበቅልና ሊቃውንት እንዳይወጡበት “ዓይጥ ይውረርሽ፣ በቂ አዝመራ አይብቀልብሽ፣ ሊቃውንትም አይውጡብሽ” ብሎ ረገመው፤ እርግማኑም ደረሰ

ሀገሪቱ ቅዱስ ያሬድን ስለገረፈችው ለብዙ ዘመናት በድርቅና በተለያዩ ችግሮች ስትፈተን ኖራለች ፡፡ በቦታውም ከትልቅ ማዕርግ የደረሰ ሰው ሳይወጣባት እንደ ቆየ አባቶች ይናገራሉ ፤ ብዙ አባቶችም “የቅዱስ ያሬድን ታቦት አምጥታችኹ ቤተ ክርስቲያን ሠርታችኹ ብታቋቁሙት ረድኤቱ ይመለስላችኋል፤ መርገሙ ይሻርላችኋል እንዲሁም መታሰቢያውን ብታደርጉ ዝክሩን ብታዘክሩ ስሙን ብትጠሩ ይህ ሁሉ ችግር ይቃለልላችኋል” እያሉ ምክር ሲለግሷቸው ቆይተው በ1956 ዓ.ም በአንዲት መበለት ምክንያት ጥላጌ መስክ ላይ ምህረት ተለምኗል፡፡ ደልደለት ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ታንጾ ታቦቱ ስለገባ ፍጹም በረከት ወርዶላታል ፡፡ ከዚያን ወዲህ ሊቃውንት መውጣት ጀመሩ፣ አይጥም ጠፋ ፡፡ በየጊዜው ዝናም ለዘር ጠል ለመከር የማይለያት፣ ጥቂት ቢዘሩ ብዙ የሚያመርቱባት፣ ሰው ሁሉ በፍጹም ተድላ የሚኖርባት ሀገር ኾናለች ፡፡ ይኸውም የጻድቁ ይቅርታ መኾኑ ታውቆ በዕለተ ሰንበት መዝሙር በየወሩ መኀሌት እየተቆመ መታሰቢያው ይደረጋል ፡፡ በዙሪያው ያሉ መምህራንና መዘምራን ካህናት ስላሉ ክብረ በዓሉ በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡



**ደልዳሊት ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን**

### የዐፄ ገብረ መስቀል ተመሥጦ

የቅዱስ ያሬድ ዜማ እንዴት ሁሉንም ይመሥጥና ወደ አርያም በመንፈስ ይወስድ እንደነበር ለማስረዳት በመጽሐፈ ገድሉም ኾነ በሌሎች መጻሕፍት የተመዘገቡ ታሪኮች አሉ፡፡ ቅዱስ ያሬድ በቅድስት አኲሱም ወንበር ዘርግቶ፣ ጉባኤ አስፍቶ ደቀ መዛሙርቱን እያስተማረ ሲኖር በጾመ ፵ ሱባዔ ላይ ሳለ አንድ ቀን በምኲራብ ሰሞን ስለምናኔው እያስታወሰ በተመስጦ ሲዘምር የዜማው ጣዕም እንኳን ሌላውን ራሱን እጅግ ይመሥጠው ነበር፡፡ በጣዕመ ዝማሬው ተመሥጦ ሲያዳምጥ የነበረው ኢትዮጵያዊው ንጉሥ የዐፄ ካሌብ ልጅ ዐፄ ገብረ መስቀል ዐይን ዐይኑን እየተመለከተ ሳይታወቀው በመስቀል ሰላጢኑ (በበትረ መንግሥቱ ዘንግ) ጫፍ የቅዱስ ያሬድን እግር ወጋው፡፡



**የዐፄ ገብረመስቀል ተመሥጦ**

ቅዱስ ያሬድ ግን ከሰማያት የተገኘች ቃለ ማኅሌቱን እስኪፈጽም ድረስ ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ሕመሙ ሳይታወቀው ቀጠለ፤ ደሙም ያለማቋረጥ ፈሰሰ፡፡ ቅዱስ ያሬድ የጀመረውን በፈጸመ ጊዜ ንጉሡ ደንግጦ በትሩን ከቅዱስ ያሬድ እግር ላይ ቢነቅለው ደሙ በኀይል ይፈስ ጀመር፡፡ ያን ጊዜ ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል የቅዱስ ያሬድን ትዕግሥት ባየ ጊዜ በመደነቅ፣ በመገረምና በመደንገጥ ዝም በማለት አፉን ይዞ ቆመና ምድራዊ ዋጋ የሚፈልግ መስሎት "ካህን ያሬድ ሆይ የምትፈልገውን የደምህን ዋጋ ጠይቀኝ" አለው፡፡ ቅዱስ ያሬድም መልሶ "የፈለግኹትን እንዳትከለክለኝ ቃል ኪዳን ግባልኝ" አለው፡፡ ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀልም የጸና ቃል ኪዳን ለቅዱስ ያሬድ ገባለት፡፡ ቅዱስ ያሬድም "ከዚህ ሐላፊ ዓለም ክብር ተለይቼ መናኝ ሆኜ እንድኖር ተወኝ አሰናብተኝ" ብሎ አሳቡን ገለጸለት፡፡

ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀልም የቅዱስ ያሬድን ቃል በሰማ ጊዜ እጅግ ደንግጦ "ወዮልኝ! ወዮልኝ! በዘመነ መንግሥቴ እግዚአብሔር የሰጠኝ እንዲህ ያለ ካህን አይገኝም ወዮ! ወየው! በሰማያዊ ጣዕመ ዜማው በተከበርኹ ፈንታ በኀዘን ባሕር ውስጥ ወደቅኹ ወዮ! ወየው! ወዮልኝ! የዐይኔ ብርሃን የራሴ ዘውድ፣ የገበዘ አኩሱም ሽልማቷ፣ ጌጧ እና ግርማ ሞገሷ" እያለ አለቀሰ፡፡ ያን ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ኀዘን ኾነ፡፡ ካህናቱ እና ሕዝቡም በሙሉ ስለ ካህን ቅዱስ ያሬድ መለየት አዘኑ፡፡ ከዚህም በኋላ ንጉሥ ዐፄ ገብረ መስቀል ያሬድ ካህን የጠየቀውን እንዳይከለክለው ከአፉ የወጣውን መሐላ አስቦ በምናኔ አሰናበተው እንጂ ሊከለክለው አልቻለም፡፡

ቅዱስ ያሬድ ካህንም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ወዳለችበት ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሁለት እጆቹን በታቦተ ጽዮን ላይ አኑሮ "ቅድስት ወብፅዕት፣ ስብሕት ወቡርክት፣ ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን መዓርገ ሕይወት"(አንቀጸ ብርሃን ፣ምዕራፍ) ብሎ በደረሰው አንቀጸ ብርሃን ጸሎት እመቤታችንን አመሰገነ፡፡

በዚህ ጊዜ እጁ በታቦተ ጽዮን ላይ ረቦ በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ ስለነበር ከመሬት አንድ ክንድ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፡፡ "ቅድስት ወብፅዕት … " የሚለውን እስከመጨረሻው በከፍተኛ ቃል በዕዝል ዜማ እየዘመረ እግዚአብሔርን እና እመቤታችንን ከአመሰገነ በኋላ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች አምላክን የወለደች እመቤታችን የቀና መንገድ እንድትመራውና እስከ ፍጻሜ ገድሉ ትረዳው ዘንድ በጸሎት ለመናት፡፡ እመቤታችንም መልሳ "ሰማያዊት ጽዮን ያደረግኻት መቅደሴን፣ በመዝሙርና በማኅሌት ምስጋና የኪሩቤልና የሱራፌል ወገን ሰማያውያን ያደረግኻቸው ልጆቹ ካህናትን እንዴት ትተህ ትሄዳለኽ" ብላ ቃል

በቃል አነጋገረችው፡፡ የመንገዱን ስንብት እስክትፈቅድለት ድረስ በለቅሶና በእንባ ዳግመኛ ለመናት፤ እርሷም እንዲሄድ ፈቀደችለት፡፡

**የቅዱስ ያሬድ ምናኔ**

ቅዱስ ያሬድ የሚመንንበት ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለደረሰ የመሰናበቱን ጉዳይ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ወጣ፡፡ ከዚያም እንደ ኪሩቤልና ሱራፌል ያደረጋቸውን መዘምራን ካህናት ለአኩሱም ጽዮን አበርክቶላት ለመሄድ ተነሣ፡፡ በዚህ ጊዜ የሚወዱት ካህናት፣ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ተከትለውት እስከ ተከዜ ወንዝ ድረስ ሸኙት፡፡ ከእርሱ በሚለዩበትም ጊዜ "ሰላመ ነሳእነ ወሰላመ ኃደግነ ለክሙ ወሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስለ ኵልክሙ፤(ሰላም፣ድጓ) ሰላምን ከእናንተ ተቀበልን ለእናንተም ሰላምን ተውንላችሁ የእግዚአብሔር ሰላምም ከሁላችሁ ጋራ ይኹን" ብሎ በዜማ ተሰናበታቸው፡፡

ዳግመኛም "ወሰላመ እግዚአብሔር እንተ ኲሉ ባቲ ተሃሉ ወትረ ምስለ ኲልክሙ፤ (ሰላም፣ጾመ ድጓ) ፍቅርና ስምምነት ሁሉ ያለባት የእግዚአብሔር ሰላምታ ሁል ጊዜ ከሁላችሁ ጋራ ትኑር" ብሎ በጣዕመ ዜማው መረቃቸው፡፡


ካህናቱም ይህን ሰምተው አለቀሱ፡፡ እርሱም ከእነርሱ ጋራ አለቀሰ፡፡ በዚሁ ጣዕመ ዜማው የመጨረሻ ቡራኬውን ሰጣቸውና እርስ በእርሳቸው ተሳስመው ተሰነባብተው ከእርሱ በመለየታቸው እያዘኑና እየተከዙ ወደ ሀገራቸው አኩሱም ተመለሱ፡፡ እርሱ ግን የተከዜን ወንዝ ተሻገረ፡፡ የወንዙ ፏፏቴና ጎርፍ እንደሚጮህ አንበሳ ሲጮህ በሰማ ጊዜ "አኀለፍኮሙ በእግር እንተ የብስ ማእከለ ባሕረ ተከዜ . . .፤ (ዕዝል፣ድጓ) በተከዜ ባሕር መካከል በእግር እንደሚሻገር በደረቅ አሻገርካቸው. . ." እያለ በረቀቀ ምስጢር እግዚአብሔርን በማመስገን እየዘመረ ሲሄድ አንዲት ሴት ውሃ ቀድታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ድምፁን ሰምታ ወይ ቃል! ወይ ቃል! እንዴት አንጀት ይበላል! ምንኛስ ያሳዝናል! ብላ ደጋግማ በማድነቅ ስለ ተናገረች ቅዱስ ያሬድ ቆሞ የዘመረባት ቦታ "ወይ ቃል" ተብላ ተጠራች፡፡ ዛሬ ይህች ቦታ ጎንደር ክፍለ ሀገር ደባርቅ አካባቢ ***"ወይ ቃል"*** ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራለች፡፡

ቅዱስ ያሬድ ወደ ስሜን ተራሮች ሄዶ ጠለምት ወጥቶ ብርድ በጸናበት በረዶ በተከማቸበት ሳኔር ተብሎ በሚጠራ በሐዊ ዐምባ ጽሙና ይዞ ተቀመጠ፡፡ በዚያም በብዙ ትጋት በጾምና በጸሎት ይልቁንም በስብሐተ እግዚአብሔር ብቻ ተወስኖ ጉባኤ ዘርግቶ፣ ትምህርት አስፍቶ ከሱራፌል መላእክት እንደተማረው አድርጎ ከጠለምት፣ከስሜን፣ ከአገውና ከሌላ ሀገር ወደ እርሱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ ማኅሌተ መላእክትን እያስተማረ ኖረ፡፡

ከብዙ ዘመን በኋላም ያስተማራቸው የአኩሱም ጽዮን ካህናት ሊጠይቁት መጥተው ቀርበው እጅ በነሱት ጊዜ "አኃውየ ሰላም ለክሙ ወበሰላም እኤምኀክሙ ወከልሐ ወይቤ አኃውየ ሰላም ለክሙ ወበሰላም ቅድስት እኤምኀክሙ አምኃክሙኒ ፍሥሓ ወሰላም አንትሙኒ ተአማኀክሙኒ ወአነ አማኀኩክሙ አምኀ ሰላም፤ (ሰላም፣ጾመ ድጓ) ወንድሞቼ ሰላም ለእናንተ ይኹን በሰላም እጅ እነሳችኋለኹ፤ ዳግመኛም አሰምቶ ተናገረ ሰላም ለእናንተ ይኹን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሰላም እጅ ትነሣችኋለች፤ ሰላምታችኹም ደስታና ሰላም ነው፤ እናንተም ሰላም አላችኹኝ እኔም ሰላም አልኋችኹ" እያለ በዓራራይ ዜማ በናፍቆት ከተቀበላቸው በኋላ መላልሶ ሳማቸው፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ አገራቸው አኩሱም ለመመለስ በተነሡ ጊዜ ሊሰነባበቱና ቡራኬውን ሊቀበሉ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ከፊቱ ቆሙ፡፡ ወዲያውኑ ቅዱስ ያሬድ በቃለ ትሕትና "አኃውየ ሰላም ለክሙ ወበሰላም እኤምኀክሙ ዝክሩኒ ወትረ በጸሎትክሙ እስመ ብዙኀ ትረድእ ጸሎተ ጻድቅ ወስእለተ ጻድቅ ይፈጽም ለክሙ ተስፋክሙ ሰላመ አቡየ ምስለ ኩልክሙ፤ ወንድሞቼ ፥ሰላም ለእናንተ ይኹን፤ በሰላምም እሰናበታችኋለኹ ፤ዘወትር በጸሎታችኹ አስቡኝ፤ የጻድቅ ጸሎት ብዙ ትረዳለችና የጻድቅ ልመናም ተስፋን ትፈጽማለች ፤የአባቴ ሰላም ከሁላችሁ ጋራ ይሁን" እያለ ምስጢሩን አስማምቶ በዓራራይ ዜማ ባርኮ አሰናበታቸው፡፡

ካህኑ ቅዱስ ያሬድ ጽሙና አጽንቶ በስሜን ገዳም በጠለምት አምባ ሲቀመጥ ቀድሞ በልጅነቱ በቤተ ቀጢን (ጉባኤ ቤት) አኩሱም ትምህርት ቤት ሲማርና ኋላም ዜማ በደረሰበት ዘመን የሚያውቃቸውና የሚያከብራቸው ከ9ኙ ቅዱሳን አንዱ አባ ጰንጠሌዎን ዘጾማዕት፣ ሰማዕቱ ጰንጠሌዎን ዘአኮሬዎን (ጥቅምት 6 ቀን)፣ አባ ይምአታ ዘገርዓልታ (ጥቅምት ፳8 ቀን)፣ አባ ገሪማ ዘመደራ (ሰኔ 07 ቀን) ማረፋቸውን ባለበት ኾኖ በጸጋ ስላወቀ አኩሱም ሳለ ትሩፋታቸውንና ቅድስናቸውን ስለሚያውቀው በዐረፉበት ቀን በየዓመቱ የሚዘመርላቸውን መዝሙር አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይልቁንም አባ ገሪማ በትምህርታቸው የበለጡ ስለነበሩ ዕውቀታቸውን እያብራራ በመዝሙር፣ በዝማሬና በመዋሥዕት፣ ውስጥ በስፋት አንስቷቸዋል፡፡ የስሜን ሰዎች ድጓውን በዚህ ሥፍራ ደረሰው የሚሉት ይህን አብነት አድርገው ነው፡፡



**ጠለምት ደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ ዋሻ ገዳም**

ቅዱስ ያሬድ በንጉሥ ገብረ መስቀል ፈቃድ ከትውልድ ሀገሩ አኵሱም መንኖ ከወጣ በኋላ ትዕግሥቱን እያዘወተረ ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ በማስተማር በገዳመ ስሜን ኖረ፡፡ የመድኀኒታችንንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም (ቅዱስ ቊርባን) ለመቀበልና ቅዱሳት ገዳማትን ለመሳለም በፈለገ ጊዜ በሠረገላ ብርሃን ተጭኖ አኵሱም ደርሶ ቅዱስ ቊርባንን ተቀብሎ ሌሎች ገዳማትንም ይሳለም ነበር፡፡ በዚያውም ንጉሥ ዐፄ ገብረ መስቀል ያሳነፃት አርያማዊት መቅደስ የተባለችውን ደብረ ዳሞን ጎብኝቶ ሳይውል ሳያድር በሠረገላ ብርሃን ተጭኖ ወደ ማደሪያው ገዳመ ስሜን ይመለስ ነበር፡፡

**የቅዱስ ያሬድ ቃል ኪዳን ተቀብሎ መሠወር**

ቅዱስ ያሬድ ካህን ዘመኑን ሁሉ በመላእክት ማኅሌት እግዚአብሔርን በማገልገልና ይህን ማኅሌት ለሚከተሉት ደቀ መዛሙርት በማስተማር ዘመኑን ፈጽሞ ከ፳2 ዓመታት በላይ በምናኔ ታግሦ በገድሉና በጣዕመ ዜማው ጸላኤ ሠናያትን ድል አድርጎ ከዚህ ዓለም ድካምና መከራ የሚያርፍበትና ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ በተጠምት ዋሻ ውስጥ የሚሠወርበት ቀንና ሰዓት መድረሱን

በጸጋ በዐወቀ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ "ይቤ ጳውሎስ ኃላፊ ንብረቱ ለዝንቱ ዓለም አኃውየ አስተፋጥኑ ገቢረ ሠናየ አንሰ በድረየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ ሠለጥኩ እንከሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊል ዘየዓሥየኒ መኰንነ ጽድቅ፤ጳውሎስ የዚህ ዓለም ንብረት ኃላፊ ነው አለ፤ ወንድሞቼ መልካም ለማድረግ ተፋጠኑ እኔ ሩጫዬን ጨረስኹ፤ ሃይማኖቴን ጠበቅኹ ከእንግዲህ ወዲህ የእውነት ገዢ የሚሰጠኝ አክሊል ይቆየኛል" (2ኛ ጢሞ. 4፥7-8) እያለ በሚያራራ ቃል ምክሩን ሰጥቶ ተሰናበታቸው፡፡ እነርሱም ምክሩን ተቀብለው "አባ አቡነ፣ አባ መምህርነ አይቴ ተሐውር ወለመኑ ተኀድገነ፤ አባታችን መምህራችን ወደ የት ትሔዳለኽ? ለማንስ ትተወናለኽ?" እያሉ ሲያዝኑ ሲያለቅሱ በአንድ ዋሻ ውስጥ ገብቶ ግንቦት 11 ቀን ተሠወረ፡፡